# የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር---

# ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

## መግቢያ

የወንጀል ሕግ አላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግስት፣ የህዝቦቹን፣ የነዋሪዎቹን፣ ሰላም፣ ደህንነት፣ ስርአት፣ መብትና ጥቅም ማጠበቅና ሚረጋገጥ ነው፡፡

የወንጀል ሕጉ ከዚህ በላይ የተመለከተውን አላማ ለማሳካት ዋና ግቡም ወንጀል እንዳይፈጸም መከላከል ሲሆን፣ ይህንንም የሚሳካው ለህብረተሰቡ ሰላምና ደህንነት አደጋ የሆኑ የወንጀል ተግባራትን እና እነዚህን ሜጸም የሚያስከትለውን ቅጣት ሰዎች አውቀው ከወዲሁ ከህገወጥ ተግባር እንዲቆጠቡ ማስተማርና ማሳወቅ ሲሆን፣ ይህ ሳይሳካ ቀርቶ ጥፋት አድራጊዎች ሲኖሩ እነዚህን ተገቢውን ቅጣታቸውን እንዲያገኙ በማድረግ ሌላ ወንጀል ከመፈጸም እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈጽሙ እርምጃዎች እንዲወሰዱባቸው በማድረግ ነው፡፡

ቅጣት የወንጀል መከላከል ግቡን እንዲያሳካ ለእያንዳንዱ የወንጀል ድርጊት በወንጀል ህጉ ማነሻና ጣሪያ የተቀመጠ ሲሆን፣ ከዚህ በተጨማሪ በእነዚህ የቅጣት ማነሻና ጣሪያ መነሻት ቅጣቱን ለመወሰን የሚያገለግሉ መርሆዎችንና መመሪያዎችን የያዙ ጠቅላላ የቅጣት አወሳሰን ድንጋጌዎችም በወንጀል ህጉ ተካተው ይገኛሉ፡፡

ይሁንና በወንጀል ህጉ ስለቅጣት አወሳሰን የተቀመጡት ድንጋጌዎች በፍርድ ቤት የሚሰጡ ቅጣቶች ወጥነት፣ ተመዛዛኝነት፣ ፍትሀዊ እንዲሆኑ ከማድረግ አንጻር ክፍተቶች እንዳላቸው ግልጽ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ለተመሳሳይና ተቀራራቢ የወንጀል አፈጻጸሞች ተመሳሳይና ተቀራራቢ ቅጣት ለመጣል አስቸጋሪ እንደሚሆን መገመት ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል በፍርድ ቤቶቻችን የሚሰጡ የቅጣት ውሳኔ መዝገቦችን ስንመለከት ቢያንስ ክፍተት ባለውም የቅጣት አወሳሰን መርሆዎችን መሰረት አድርገው የሚሰሩ ባለመሆናቸው በቅጣት አወሳሰን ያለውን ችግር እንዲባባስ እንዳደረጉት የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡ በጣም የሚበዙትን የቅጣት ውሳኔ መዝገቦችን ብንመለከት ፍርድ ቤቶች ቅጣቱን ለመወሰን፣

- ማኅሻ የቅጣት ማጡኑ ስንት እንደሆነ፣
- በማክበጃነት የተቀማጡት ምክንያቶች ቅጣቱን በማክበድ ያላቸው አስተዋጽኦ እንዲሁም ማቅለያ ምክንያቶች እንዴት አገልግለው ቅጣቱ እንደቀለለ፣

ለማወቅ የሚያስችሉ አይደሉም፡፡ በአጭሩ ቅጣቱን ለመወሰን በቀረቡት ምክንያቶችና በተወሰነው ቅጣት መካከል ያለው ምክንያታዊ ግንኙነትን ለማስረዳት የሚያስችሉ አይደሉም፡፡ አብዛኛውን ጊዜ በወንጀል ህጉ ቁጥር 88 (2) ያሉትን ለቅጣት አወሳሰን ሊታዩ የሚገባቸውን ነጥቦች በቅጣት ውሳኔ ውስጥ እንዲሁ ከማዘርዘር ባሻገር ትኩረት እና ተገቢ ትርጉም ሰጥተዉ የሚታገብሩበት ሁኔታ አይታይም፡፡

ስለሆነም የቅጣት ውሳኔ ማዝገቦች ሲገማሙ በወንጀል ህጉ ያለውን ክፍተት ለማዘጋት የሚያስችሉ ሊሆኑ ይቅርና እንዲያውም የወንጀል ህጉ የቅጣት አወሳሰን ድንጋጌዎችን ጨርሶውኑ በመተው በቅጣት አወሳሰን የዘፈቀደ አሰራር እንደነገሰ የሚያስረዱን ናቸው፡፡

ከዳኛ ዳኛ በሚደረሰው የቅጣት ማጠን ማለያየት መኖሩን የወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች ሊያስቀሩት ባይችሉም፣ ነገር ግን ህጉ ያስቀመጣቸው ስነስርአቶች ማለትም በቅድሚያ መኅሻ ቅጣቱን መወሰን፣ ቀጥሎ ማክበጃ ምክንያቶችን ተመልክቶ ቅጣቱን ማክበድ፣ በመቀጠልም ማቅለያ ምክንያቶችን ተመልክቶ ቅጣትን ማቅለል በሚል በህጉ ላይ የተቀማጠው መመሪያ ተከብሮ አናገኝም፡፡ ስለሆነም በህጉ ላይ ያለውን ክፍተት ከማሟላት ይልቅ፣ ወጥነት የሌለው መያዣና መጨበጫ የሌለው የቅጣት አወሳሰን ልምድ ያለን መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

ቅጣትን ለመወሰን የሚያስችል ዝርዝር መመሪያ ባለመኖሩም የቅጣት ማክበጃም ሆነ ማቅለያ ለማቅረብ፣ በማስረጃ ለማስረዳት ይህ ነው የሚባል ተገቢው ዝግጅትም ስለማይደረግ፣ ውሳኔው በህሊና ግምት እንደሚወሰን መገመት አያዳግትም፡፡ በዚህ አይነት የአወሳሰን ስርአት ውስጥ ወጥነት፣ ምክንያታዊነትና ተመጣጣኝነት ያለው የቅጣት ውሳኔ እንዲኖር መመኘት ህልም ነው፡፡ በሆነ አጋጣሚ ተመሳሳይ ለሆኑ ወንጀሎች ተመሳሳይ ቅጣት ቢጣል የአጋጣሚ ከመሆን አልፎ ሌላ ሊሆን አይችልም፡፡

ስለሆነም፣

1. በወንጀል ህጉ የተቀማጡት የቅጣት መኅሻና መድረሻ እንዲሁም ስለቅጣት አወሳሰን የተቀማጡት ድንጋጌዎች በራሳቸው ወጥነት፣ ተመጣጣኝነት፣ ፍትሀዊና ተገማችነት ያለውን ቅጣት ለማስጠት የሚያስችሉ አይደሉም፡
2. በተጨባጭ እየተሰሩ ያሉ ቅጣት የተሰጠባቸው ማዝገቦችም በቅጣት አወሳሰን ወጥነት፣ ተመጣጣኝነት፣ ፍትሀዊነትና ተገማችነት ያለው ቅጣት እየተሰጠ እንደሆነ አያማለክቱም ብቻ ሳይሆን፣ የተዘበራረቁና ለማስረዳት የሚያስቸግሩ ቅጣቶችን የሚሰጡ ሆነው ይታያሉ፡፡

የቅጣት አወሳሰን አንድ ወጥነት እና ትክክለኛነት ጠቃሚነቱ በአንድ ጉዳይ ጥፋተኛ ተብሎ ለሚቀጣ ወንጀል ፈፃሚ ብቻ ሣይሆን፣ በወንጀሉ በቀጥታ ተጠቂ ለሆኑት የግል ተበዳዩች እና ተመሣሣይነት እና አንድ ወጥነት በጐደለው የቅጣት አወሳሰን ምክንያት በወንጀል የፍትህ አስተዳደሩ ላይ እምነት ለሚያጣው ለጠቅላላው የህብረተሰብ ክፍል ነው፡፡

ዴሞክራሲያዊ ስርዓትና መልካም አስተዳደር ለማንባት እንዲሁም ልማት እና እድገትን ለማፋጠን እየተደረጉ ያሉትን ጥረቶች አጠናክሮ ለማስቀጠል ይቻል ዘንድ በህግ የበላይነት ላይ የተመሰረተ ፍትሃዊ፣ ተደራሽ፣ ቀልጣፋ፣ ተገማችና ሚዛናዊ የሆነ ግልጽነት እና ተጠያቂነትን የሚከተል ወጤታማ የፍትህ አሰጣጥ እንዲኖር የቅጣት አወሳሰን ወጥነትና ትክክለኛነት ያለው መሆን የግድ ይላል፡፡

የቅጣትን አንድ ወጥነት እና ትክክለኛነት ሚረጋገጥ ህገ መንግስታዊ እና ከመሠረታዊ መብቶች በተለይ ከእኩልነት መብት ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው፡፡ ሁሉም ሰዎች በህግ ፊት እኩል መሆናቸው በመካከላቸውም ማንኛውም ዓይነት ልዩነት ሣይደረግ በህግ እኩል ጥበቃ እንደሚደረግላቸው በህገ መንግስቱ አንቀጽ 25 በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ስለዚህ ለምሣሌ ከህጉ መንፈስ ውጭ የተጣለ ከባድ ቅጣት ቢኖር በዘፈቀደ የተወሰነ ብቻ ሣይሆን የዜጎችን እኩል የህግ ጥበቃ የማግኘት መብት የሚጥስ እና የዳኝነት አካሉም በህገ መንግስቱ የተመለከቱ መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶቻቸው የማክበርና የማስከበር ግዴታውን አለመወጣቱን ስለሚያመለክት የቅጣት ውሣኔው ህገ መንግስታዊ ነው አይባልም፡፡

ስለሆነም በፍርድ ቤቶቻችን ሲሰጥ ከነበረው የቅጣት አወሳሰን ተሞክሮ በመነሳት፣ በቅጣት አወሳሰን የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት የወንጀል ህጉ ያስቀመጣቸውን የቅጣት አወሳሰን መርሆዎችና ድንጋጌዎች በራሳቸው በቂ ስላልሆኑ፣ እነዚህን መርሆዎችና ድንጋጌዎች በሚደግፍና በሚያሟላ መልኩ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በቅጣት አወሳሰን ትክክለኛነትንና ወጥነትን ለሚረጋገጥ የሚያስችል የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ማውጣት እንዲችል በዚሁ የወንጀል ህግ አንቀጽ 88(4) ስልጣን ሰጥቶታል፡፡

መመሪያውን የማውጣቱ መርህ የሚጠይቀው በተመሣሣይ ወንጀል ጥፋተኛ የተሰኙ እና ተመሣሣይ የቅጣት ማክበጃም ሆነ ማቅለያ ምክንያቶች የቀረበባቸው እና የግል ሁኔታዎቻቸው ተመሳሳይ የሆኑ አጥፊዎች ተመሣሣይ ወይም ተቀራራቢ ቅጣት ሊጣልባቸው የሚገባ መሆኑን ነው፡፡

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወንጀል ህጉ በተሰጠው ስልጣን መሰረትም በአጠቃላይ ከ80 በመቶ በላይ የሚሆነውን የፍርድ ቤት መዝገቦች የሚይዙትን፣ በተደጋጋሚ የወንጀል ድርጊት እየተፈጸመባቸው የሚቀርቡትን የወንጀል ጉዳዮችን በማምረጥ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ የማዘጋጀት እንቅስቃሴ ጀምሮ በእነዚህ በተመረጡ የወንጀል ጉዳዮች ላይ መመሪያውን ለማውጣት ጥናት እንዲያደርጉ ከፌደራልና ከክልል በተወጣጡ ባለሙያዎች ጥናት ሲደረግ የቆየ ሲሆን፣ እነዚህም ባለሙያዎችም የተለያዩ አማራጮችን የያዙ የጥናት ሰነዶች አቅርበዋል፡፡

በእነዚህ በቀረቡት የተለያዩ የጥናት ሰነዶች ላይም አወደጥናት በማድረግ ግብአት የተገኘ ሲሆን፣ ግብአቶቹን ማሰረት በማድረግም ለቅጣት አወሳሰን የሚረዳ መመሪያ የማዘጋጀት ስራ ሲሰራ ቆይቷል፡፡

መመሪያወን ለማዘጋጀት የተለያዩ አገራት ተሞክሮን ለማየት ጥረት የተደረገ ሲሆን፣ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ አዘጋጅቶ ተግባራዊ በማድረግ ከሁሉም አገራት የተሻለ ተሞክሮ እና ልምድ ካላት አሜሪካ ልምዱን በመወሰድ ከኢትዮጵያ የወንጀል ፍትህ ስርአት ጋር በሚጣጣም መልኩ እና የወንጀል ሕጉ በቅጣት አወሳሰን የደነገጋቸወን ድንጋጌዎች በሟሟላ መልኩ ይህ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

ይህ መመሪያ በአገሪቱ የወንጀል ፍትህ አስተዳደር አዲስ በመሆኑ ለዚህ ዝግጅት የሚሆን ተሞክሮ በአገሪቱ አይገኝም፡ መመሪያወን ለማዘጋጀት የተሰሩት ጥናቶች የተሰሩት በዚህ አይነት ሁኔታ ወስጥ መሆኑን ከግምት በማስገባት መመሪያው ተግባራዊ ሲደረግ ሊያጋጥሙ የማቹሉ የአፈጻጸም ችግሮችና ወሱንነቶች ሊኖሩበት እንደሚችሉ ማመት ተገቢ ነው፡ ይሁንና መመሪያው የመጨረሻ ሳይሆን በተግባር እየተፈተነና እየዳበረ የሚሄድ ነው፡ ስለሆነም በመመሪያው ሊሳካ የታቀደው አላማ በቀጣይነት በተግባር ተሞክሮ እየዳበረና እየጎለበት መመሪያው ሊያሳካ ያሰበወን ጠንካራና ወጤታማ የወንጀል ፍትህ ስርአት የማንባት ራእዩን እንደሚያሳካ ግን የሚያጠራጥር አይሆንም፡

ስለሆነም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወንጀል ሕግ 1997 አንቀጽ 88 ንኡስ አንቀጽ 4 በተሰጠው ስልጣን ማሰረት ይህንን መመሪያ አወጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 1. ስያሜ

ይህ መመሪያ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር ------ ተብሎ ይጠቀሳል፡፡

### አንቀጽ 2. ትርጓሜ

1. ‹ፍርድ ቤት› ማለት የፌደራልና የክልል ፍርድ ቤቶችን ማለት ነው፡
2. ‹የወንጀል ደረጃ› ማለት በወንጀል አፈጻጸም ባህርያቸወና ከባደነታቸው አንጻር ለቅጣት አወሳሰን በተመሳሳይ ደረጃ ለማስቀመጥ እንዲቻል የወንጀል ድርጊት መመዘኛዎችን የያዘ ነው፡

3. ‹የቅጣት እርከን› ማለት የቅጣት መነሻና መድረሻ ያለው ፍርድ ቤት በዚህ መመሪያ መሰረት ቅጣቱን የሚወስንበት እርከን ማለት ነው፡፡

4. ‹ፍቅድ ስልጣን› [range] ማለት ፍርድ ቤቶች የወንጀል አፈጻጸሙን ልዩ ሁኔታ ከግምት በማስገባት ቅጣቱን ለመጣል የሚችሉበት በቅጣት እርከን የተቀመጠው መነሻና መድረሻ ቅጣት መካከል ያለው የቅጣት መጠን ማለት ነው፡፡

5. ‹መነሻ ቅጣት› ማለት ቅጣቱን የሚያከብዱና የሚያቀሉ ጠቅላላ እና ልዩ ምክንያቶች ታሳቢ ከመደረጋቸው በፊት በፍርድ ቤቱ የቅጣት እርከኑን መሰረት በማድረግ የሚጣል ቅጣት ነው፡፡

## አንቀጽ 3 . የመመሪያው አላማና ግብ፣

1. የመመሪያው አላማ በወንጀል ፍትህ ስርአቱ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ባረጋገጠ መልኩ ወጥነትና ተገማችነት ያለው ቅጣት የሚሰጥበትን ስርአት በመመስረት ወንጀል እንዳይፈጸም መከላከል ነው፡፡
2. መመሪያው የሚከተሉት ግቦች ይኖሩታል፡፡
   ሀ. በተቀራራቢና ተመሳሳይ የወንጀል ጉዳዮች መካከል ተቀራራቢነት ያለው የቅጣት አወሳሰን (ወጥነትን) ማረጋገጥ፣
   ለ. እንደወንጀሉ ክብደትና አደገኛነት መሰረት ተመጣጣኝ ቅጣት ያለው የቅጣት አወሳሰን ማረጋገጥ ነው፡፡

## አንቀጽ 4. መሰረታዊ ድንጋጌዎች

1. በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 189 እንደተደነገገው ፍርድ ቤቶች ቅጣት ሲወስኑ ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶችን መሰረት አድርገው ቅጣቱን ከማስላታቸው በፊት ከተጣሰው የወንጀል ድንጋጌ አንጻር የወንጀሉን ከባድነትና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ነጥቦች መሰረት በማድረግ በቅድሚያ መነሻ ቅጣቱን ይወስናሉ፣ በመቀጠልም ማክበጃ ምክንያቶችን መሰረት በማድረግ ቅጣቱን ያከብዳሉ፣ በመጨረሻም ማቅለያ ምክንያቶችን መሰረት በማድረግ ቅጣቱን ያቀላሉ፡፡
2. በቅጣት አወሳሰን ተመሳሳይና ተቀራራቢ የወንጀል ደረጃዎች መካከል ተመሳሳይና ተቀራራቢ ቅጣት ለመጣል ያስችል ዘንድ ወንጀሎችን በተመሳሳይ ደረጃ የሚያስቀምጣቸውን መሰረታዊ ባህርይ መሰረት በማድረግ የቅጣት ወሳኔ ይሰጣል፡፡
3. በየድንጋጌው ወንጀሉን የሚያቋቁመው ፍሬነገር አንድና ተመሳሳይ ቢሆንም፤ ይሁንና ከአደገኛነታቸው አንጻር፣ ወይም ከሚያደርሱት ጉዳት አንጻር ልዩነት ለደረግባቸው የሚገቡ የወንጀል ድርጊቶች እንደወንጀሉ ክብደትና አደገኛነት ደረጃ በማውጣት ቅጣት ይወሰናል፡፡

4. በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል ለእያንዳንዱ የወንጀል ድርጊት የተደነገገው የቅጣት መነሻ ትርጉም እንዲኖረው ለማድረግ እንዲቻል በድንጋጌው ከተቀመጠው መነሻ ጀምሮ እንደወንጀሉ ከባድነት መነሻው ከፍ እያለ በሚሄድ ሜልኩ ቅጣት ይወሰናል፡፡

5. በወንጀል ህጉ ልዩ ክፍል ለእያንዳንዱ የወንጀል ድርጊት የተደነገገው ጣሪያ ላይ የሚደረሰው ጠቅላላ ማክበጃ ምክንያቶች በሚኖሩበት ጊዜ መሆኑን ታሳቢ ባደረገ ሜልኩ ከፍተኛው የወንጀል ደረጃ መነሻ ቅጣቱ ይወሰናል፡፡

6. የቅጣት ማክበጃዎችና ማቅለያዎች በተመሳሳይና ተቀራራቢ ደረጃ ለሚገኙ የወንጀል ድርጊቶች ወጥነት ባለው ሜልኩ ቅጣቱን የሚያከብዱ ወይም የሚያቀሉ ይሆናሉ፡፡

7. ፍርድ ቤቶች መነሻ ቅጣቱን ለማስቀመጥ፣ እንዲሁም የቅጣት ማክበጃዎችና ማቅለያዎችን ማስረት በማድረግ ቅጣቱን ለማክበድ ወይም ለማቅለል ሲወስኑ እንደወንጀሉ ሁኔታ ሊታዩ የሚገቡ ልዩ ጉዳዮችን ታሳቢ በማድረግ በየቅጣት እርከኑ ባለው ፍቅድ ስልጣን ወስጥ አግባብነት ያለውን ቅጣት መወሰን ይችላሉ፡፡

8. በዚህ መመሪያ የወንጀል ደረጃ ያልወጣላቸው የወንጀል ድንጋጌዎችን በመጣስ የሚፈጸሙ የወንጀል ድርጊቶች ላይ የሚወሰነው ቅጣት በዚህ መመሪያ የወንጀል ደረጃ ለወጣላቸው የወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች ላይ ቅጣት ለመጣል የተቀመጡትን መርሆዎችና አሰራሮች ማስረት አድርጎ ይሆናል፡፡

9. ይህ መመሪያ የወንጀል ህጉ በቅጣት አወሳሰን ያሉትን ክፍተቶች የሚያሟላ ስለሚሆን፣ በወንጀል ሕጉ ስለቅጣት አወሳሰን ከተደነገጉት ድንጋጌዎች ጋር በተጣጣመ ሜልኩ ይተረጎማል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የቅጣት እርከኖች ሰንጠረዥ

### አንቀጽ 5. የቅጣት እርከኖች ሰንጠረዥ

በዚህ መመሪያ ማስረት ቅጣት የሚጣለው ለተመሳሳይና ተቀራራቢ ወንጀሎች ተመሳሳይ እና ተቀራራቢ ቅጣት ለመጣል እንዲቻል፣ እንዲሁም የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶች ቅጣቱን በተመሳሳይ ማጠን እንዲያከብዱ ወይም እንዲቀንሱ ለማድረግ እንዲቻል ከዚህ መመሪያ ጋር በአባሪነት ተያይዞ በሚገኘው የቅጣት እርከን ሰንጠረዥ ማስረት ነው፡፡

### አንቀጽ 6. ነጻነትን የሚያሳጡ ቅጣቶች እርከን ሰንጠረዥ

1. ነጻነትን የሚያሳጡ ቅጣቶች እርከን ሰንጠረዥ ሜት ከቀላል እስራት እስከ ሞት ቅጣት ድረስ ያለውን ያካተተ ነው፡፡

2. ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ሲባል በወንጀል ህጉ በተመለከተው ማስረት ከዝቅተኛው ቅጣት (1 ቀን የግዴታ ስራ) እስከ ከፍተኛው ቅጣት ሞት ድረስ የሚደርስ 39 የቅጣት እርከኖች ያሉት ሰንጠረዥ ተዘጋጅቷል፡፡ (አባሪ አንድን ይመልከቱ)

3. ሰንጠረዡ ሲዘጋጅ ለእያንዳንዱ የቅጣት እርከን መነሻና መድረሻ ያለው ሲሆን፣ የሚከተሉትን ማስረተ ሀሳቦች ማስረት ባደረገ መልኩ የተዘጋጀ ነው፡፡

ሀ. የቅጣት መነሻቸው ከአንድ አመት በታች ለሆኑ የቅጣት እርከኖች በመነሻውና በመድረሻው መካከል ቢያንስ የሶስት ወር ፍቅድ ስልጣን (range) እንዲኖር ሆኖ ተዘጋጅቷል፡፡

ለ. ከቅጣት እርከን 12 ጀምሮ በመነሻውና በመድረሻው መካከል ያለው ፍቅድ ስልጣን (range) ስድስት ወር እንዲሆን ተደርጓል፡፡

ሐ. ከቅጣት እርከን 16 ጀምሮ በመነሻውና በመድረሻው መካከል ያለው ፍቅድ ስልጣን (range) የመነሻውን ሃያ በመቶ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

መ. በየደረጃው ያለው የቅጣት እርከን መነሻ ሲቀመጥ፣ ከቅጣት እርከኑ ዝቅ ብሎ ከነበረው የቅጣት እርከን አማካይን መነሻ በማድረግ የቅጣት መነሻና መድረሻው ተወስኗል፡፡[1]

ሠ. በወንጀል ህጉ ቅጣቱ ከመነሻው እንደሚጀምር የተቀመጠ ስለሆነ፣ ለስሌቱ እንዲቀል የዝቅተኛው የቅጣት እርከን አማካዩ ብዘውን ጊዜ በወንጀሉ ከተቀመጡት መነሻዎች (1 አመት፣ 3 አመት፣ 5 አመት፣ 7 አመት፣ 10 አመት፣ 15 አመት) ጋር ያልተራራቀ በሆነ ጊዜ እነዚህ የቅጣት እርከኑ መነሻዎች እንዲሆኑ ተደርገዋል፡፡

ረ. በወንጀል ህጉ ቁጥር 103(1) እስከ 6 ወር የሚደርስ ቀላል እስራት እስከ 6 ወር በሚደርስ የግዴታ ስራ ሊቀየር እንደሚችል ስለሚያስቀምጥ፣ ለዚህ መመሪያ አላማ የአንድ ቀን እስራት ከአንድ ቀን (8 ሰአት) የግዴታ ስራ ጋር ተመጣጣኝ ተደርጎ ተወስዷል፡፡ ስለሆነም የእስራት ቅጣቱ በማቅለያ ምክንያት የሚቀነስ ከሆነ ተቀንሶ በተደረሰበት የእስራት ቀናት ልክ የግዴታ ስራ እንዲሰራ ሊወሰን በሚችል መልኩ የቅጣት እርከኑ ተዘጋጅቷል፡፡

---

[1] ለምሳሌ የቅጣት እርከን 12 የቅጣት መነሻና መድረሻ ከ2 አመት እስከ 2 አመት ከ6 ወር ቢሆን፣ የቅጣት እርከን 13 የቅጣት መነሻ የዚህ አማካይ የሆነው 2 አመት ከ3 ወር ይሆናል ማለት ነው፡፡

ሰ. በቅጣት ማቅለያ ጊዜ የእስራት ቅጣት ወደመቀጮ እንደሚቀየር በወንጀል ሕግ አንቀጽ 179 የሚደነግግ በመሆኑ ወደመቀጮ ሲቀየር ስንት ሊሆን እንደሚችል በሚያሳይ ሜከም የቅጣት እርከኑ ተዘጋጅቷል፡፡

## አንቀጽ 7. የገንዘብ መቀጮ ሰንጠረዥ

1. በወንጀል ህጉ አንቀጽ 90(2) የተደነገጉትን ማስፈርቶች ማስረት በማድረግ የወንጀሉን ክብደት ከግምት ባስገባ ሜሉ የገንዘብ መቀጮ ጣሪያዎችን የሚያሳይ የቅጣት እርከን ሰንጠረዥ ተዘጋጅቷል፡፡ (አባሪ ሁለትን ይሜከቱ)

2. በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 90(2) ማስረት የገንዘብ መቀጮን ለመወሰን የወንጀል አድራጊው የገቢ ማጠን፣ ሀብቱ ወዘተ ከግምት ስለሚገባና ከእነዚህ ማስፈርቶች አንጻርም መቀጮ የሚጣልበት ሁኔታ ሊኖር ስለሚችል፣ በወንጀል ህጉ ከተቀማጠው ጠቅላላ የመቀጮ ወለል ሌላ መነሻ የመቀጮ ቅጣት አልተቀማጠም፡

3. ፍርድ ቤቶች የገንዘብ መቀጮውን ሲወስኑ ከጣሪያው ሳይበልጥ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 90(2) የተማለከቱትን ታሳቢ በማድረግ ይወስናሉ፡፡

4. በወንጀል ህጉ አንቀጽ 92 በተደነገገው ማስረት ወንጀሉ በአፍቅሮ ንዋይ የተፈጸመ በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቶች በመቀጮ ቅጣት እርከን የተቀማጠውን ጣሪያ በአስር እጥፍ በማሳደግ በወንጀል ሕጉ ከተማለከተው ጣሪያ ሳይበልጥ የመቀጮውን ማጠን ሊወስኑ ይችላሉ፡፡

# ክፍል ሶስት

# የወንጀሉን መነሻ ቅጣት ስለሚወሰንበት ሁኔታ

## ንኡስ ክፍል አንድ

## እንደወንጀሉ ክብደት ደረጃ የወጣላቸው የወንጀል አይነቶች

### ርእስ አንድ

### በማግስት ስራ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፣

## አንቀጽ 8. በስልጣን አለአግባብ ማገልገል (የወንጀል ሕግ 407)

1. በዚህ መመሪያ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 407 በስልጣን አለአግባብ መገልገል ወንጀል ተከሰው ጥፋተኝነታቸው በፍርድ ቤት በተረጋገጠባቸው ወንጀል አድራጊዎች ላይ ቅጣት የሚወሰነው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡
2. በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 407 መሠረት ቅጣትን ለመወሰን በድንጋጌው ንኡስ አንቀጽ 2 ውስጥ ያሉት መሥፈርቶችን ማሇትም የስልጣን ደረጃው፣ በወንጀሉ የተገኘው ጥቅም ወይም የደረሰ ጉዳት፣ እና ወንጀሉ የተፈጸመበት አላማ መሠረት በማድረግ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ አስራ ሁለት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ (አባሪ ሶስትን ይመልከቱ)
3. ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም፡
   ሀ. ‹ከፍተኛ ስልጣን› ማሇት በተሻሻለው የፌዴራል ስነምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን አዋጅ ቁጥር 433/97 አንቀጽ 2 ንኡስ አንቀጽ 5 ውስጥ የተካተቱት ባለስልጣኖች ያላቸው ስልጣን ማሇት ነው፡፡
   ለ. ‹መካከለኛ ስልጣን› ማሇት በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ‹ሀ› ውስጥ የሚካተቱ ነገር ግን ወሳኝ የሚወስኑ የስራ ሀላፊነት ቦታዎች ማሇትም የመምሪያ ሀላፊዎች፣ የስራ ሂደት መሪዎች፣ ለመስሪያ ቤቱ የበላይ ሀላፊው ተጠሪ የሆኑ ሀላፊዎች፣ የዞን ሀላፊዎች፣ የወረዳ ሀላፊዎችና በዞንና በወረዳ መስተዳድሮች መምሪያ ሀላፊዎችንና ከእነዚህ ጋር ተመሣሣይ ስልጣን ያላቸውን ያካትታል፡፡
   ሐ. ‹ዝቅተኛ ስልጣን› ማሇት መካከለኛ የስልጣን ሀላፊነት በሚለው ውስጥ የሚካተቱ ዝቅተኛ የስራ መደብ ላይ የሚገኙ የመንግስት ሰራተኞችን ስልጣን ማሇት ነው፡፡
   መ. ‹ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት› ማሇት በወንጀል ድርጊቱ የተገኘው የገንዘብ ጥቅም ወይም የደረሰው ጉዳት ከብር 100000 በላይ ከሆነ ነው፡፡
   ሠ. ‹መካከለኛ ጥቅም/ጉዳት› ማሇት በወንጀል ድርጊቱ የተገኘው ጥቅም ወይም የደረሰው ጉዳት ከብር 10000 በላይ እስከ ብር 100000 ከሆነ ነው፡፡
   ረ. ‹ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት› ማሇት የደረሰው ጉዳት ወይም የተገኘው ጥቅም እስከ ብር 10000 ከሆነ ነው፡፡
   ሰ. ‹ከባድ አላማ› ማሇት በአፍቅሮ ንዋይ፣ በብቀላ (ሌላውን ሰው ለመጉዳት በማሰብ ብቻ፣)፣ በማን አለብኝነት፣ አጉል ትምክህት፣ ሌላ ጥፋትን መሸፈንን ያካተተ አላማን ወይም ከእነዚህ ጋር ተመሣሣይነት ያላቸው ምክንያቶችን ያካተተ ነው፡፡
   ሸ. ‹በችግር› ማሇት ወንጀሉን የፈጸመው በደረሰበት ከፍተኛ የቁሳዊ እጦት ወይም በበላይ ሀላፊ ተጽእኖ የተፈጸመ ከሆነ ነው፡፡
4. በተፈጸመው ወንጀል የተገኘውን የገንዘብ ጥቅም ወይም ጉዳት በገንዘብ ገምቶ ማስቀመጥ የሚቻል በሆነ ጊዜ ‹ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት› በሚለው ውስጥ የሚካተት ይሆናል፡፡

5. ተቃራኒ ማስረጃ እስካልቀረበ ድረስ ወንጀሉ በከባድ አላማ የተፈጸመ እንደሆነ ተደርጎ ይገመታል፡፡

6. ፍርድ ቤቱ ወንጀሉ የተፈጸመበት አላማ በተመለከተ ከባድ በሚል ከተዘረዘሩት በላይም የከፋ ነው ብሎ ባመነ ጊዜ (ለምሳሌ ወንጀሉ የተፈጸመው የአገርን ምስጢር አሳልፎ ለመስጠት ሲሆን)፣ የወንጀል ደረጃውን ከዚህ ቀጥሎ በተመለከተው መሰረት ያሳድገዋል፡፡

ሀ. በወንጀል ደረጃ 1 እና 2 የነበሩት የወንጀል ደረጃ 7 ይሆናሉ፡፡[2]

ለ. በወንጀል ደረጃ 3 እና 4 የነበሩት የወንጀል ደረጃ 8 ይሆናሉ፡፡

ሐ. በወንጀል ደረጃ 5 እና 6 የነበሩት የወንጀል ደረጃ 9 ይሆናሉ፡

መ. በወንጀል ደረጃ 7 እና 8 የነበሩት የወንጀል ደረጃ 11 ይሆናሉ፡፡

ሠ. በወንጀል ደረጃ 9 እና 10 የነበሩት የወንጀል ደረጃ 12 ይሆናሉ፡፡

# ርእስ ሁለት

# በሰው ሕይወት፣ አካልና ጤንነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፣

## አንቀጽ 9. በሰውአካልና ጤንነትላይየሚፈጸም ወንጀል (555-560)

1. በዚህ መመሪያ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 555-560 ተከሰው ጥፋተኝነታቸው በፍርድ ቤት በተረጋገጠባቸው ወንጀል አድራጊዎች ላይ ቅጣት የሚወሰነው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት ነው፡፡

2. በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 555 ‹ታስቦ የሚፈጸም ከባድ የአካል ጉዳት›፣ በአንቀጽ 558 ‹ከጥፋተኛው ሀሳብ በላይ የደረሰ ጉዳት› እና በአንቀጽ 559 ንኡስ አንቀጽ 2 ‹በቸልተኝነት የሚፈጸሙ የአካል ጉዳቶች› በወንጀሉ ምክንያት የሚደርሰው የጉዳት አይነትና መጠን ተመሳይ በመሆኑ በወንጀሉ ሊደርስ በሚችለው የአካል ጉዳት መጠን እና ወንጀል አድራጊው ሞዊ ግዴታ እያለበት የተፈጸመ የወንጀል ጥሰት መሆኑን መሰረት በማድረግ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ሰባት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ (አባሪ ሶስትን ይመልከቱ)

---

[2] በወንጀል ሕጉ 407(2) በንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት የተፈጸመውን ወንጀል ወደ ንኡስ 2 አንቀጽ ከሚያደግባቸው ማክበጃ ምክንያቶች አንዱ ወንጀሉ የተፈጸመበት አላማ ከባድነት የሚል ነው፡፡ ስለሆነም ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ከባድ አላማ በሚለው ውስጥ ከተዘረዘሩት የከፋ ምክንያት ካለ አንድ የሚያከብድ ምክንያት ሆኖ በ407(1) ውስጥ የሚቀጡ የነበሩትን ወደ 407(2) የሚያሳድግ ሲሆን፣ በ407(2) ውስጥ ይወድቁ የነበሩትን ደግሞ ከአንድ በላይ ማክበጃ ምክንያት ስለሚሆር ወደ 407(3) ያሳድጋቸዋል ማለት ነው፡፡

5. በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 556 ቀላል የአካል ጉዳት ወንጀልን በተማለከተ በድንጋጌው የተማለከቱትን ማክበጃዎች ማለትም ‹ወንጀሉን ለሚፈጸም የተጠቀማበት መሳሪያ›፣ ‹የማያ ግዴታን በመተላለፍ የተጣሰ ማሆኑ›፣ ‹ጉዳት ከደረሰበት ሰው ተጋላጭነት› አንጻር የተቀማጡት ማስፈርቶች ለዚህ መመሪያ ሲባል የቅጣት ማክበጃ የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸዋል፡፡

6. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 5 የተማለከቱት የቅጣት ማክበጃዎችን መሰረት በማድረግ እና ከአንድ በላይ ተደራርበው በሚገኙበት ጊዜ የወንጀል ደረጃወንና መነሻ ቅጣቱ ከፍ እንዲል በማድረግ ለወንጀል ሕጉ አንቀጽ 556 አራት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ (አባሪ ሶስትን ይመልከቱ)

7. በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 559(1) እና አንቀጽ 560 እያንዳንዳቸው እንደአንድ የወንጀል ደረጃ ተቆጥረው ተመድበዋል፡፡ (አባሪ ሶስትን ይመልከቱ)

8. በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 557 ንኡስ አንቀጽ ሁለት የተደነገገው ተሟልቶ በሚገኝ ጊዜ፣ በወንጀል ሕጉ 555 እና 557 መሰረት የሚደረስባቸው የቅጣት እርከኖች በሰባት ደረጃ ወደላይ እንዲያድግ በማድረግ የቅጣት እርከኑ ይወሰናል፡፡[3]

## <u>ርእስ ሶስት</u>

## <u>በንብረት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች</u>

### <u>አንቀጽ 10. የስርቆት ወንጀሎች (665 እና 669)</u>

1. በዚህ መመሪያ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 665 እና 669 ተከሰው ጥፋተኝነታቸው በፍርድ ቤት በተረጋገጠባቸው ወንጀል አድራጊዎች ላይ ቅጣት የሚወሰነው ከዚህ ቀጥሎ በተማለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት ነው፡፡

[3] በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 557(1) የተማለከቱት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ሲኖሩ፣ በአንቀጽ 556 መሰረት ተጠያቂ የሚሆን ወንጀል አድራጊ ቅጣቱ እስከ ሁለት አመት እንደሚደርስ ያማለክታል፡፡ ይሁንና በአንቀጽ 557(2) ወንጀል የተፈጸማበት ሰው ለሚረዳት የሚችል ከሆነ ቅጣቱ እስከ አራት አመት በሚደርስ እስራት እንደሚቀጣ በማስቀመጥ ቅጣቱን ስለሚጨምረው በዚሁ መሰረት የቅጣት እርከኑ ሊያድግ ስለሚገባው ነው፡፡

2. የስርቆት ወንጀል (አንቀጽ 665) በተመለከተ በወንጀሉ የተገኘው የገንዘቡ ወይም ንብረቱ ጥቅም ግምትን መሰረት በማድረግ የጥቅመኝ ሜጨሮር ታሳቢ ባደረገ ሜልኩ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ሰባት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ (አባሪ ሶስትን ይመልከቱ)

3. በወንጀሉ የተገኘው የጥቅም መጠን እስከ ብር 100 የሆነው በደንብ መተላለፍ የሚታይ ስለሚሆን በአንቀጽ 665 መሰረት የሚከተት አይሆንም፡[4]

4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ሁለት የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣

   ሀ. ወንጀሉ የተፈጸመበት ሰው ወይም ድርጅት በተሰረቀበት ሀብት/ንብረት ምክንያት የእለት ኑሮው ወይም የድርጅቱ ስራ አደጋ ላይ የወደቀ ከሆነ የገንዘብ መጠኑን መሰረት አድርጎ ከተመደበበት የቅጣት እርከን በሁለት እርከን ወደላይ ያድጋል፡፡

   ለ. የተሰረቀው ንብረት ለምሳሌ ፈንጂ፣ ተቀጣጣይ ወዘተ ከሆነ የገንዘብ መጠኑን መሰረት አድርጎ ከተመደበበት የቅጣት እርከን በሁለት እርከን ደረጃ ወደላይ ያድጋል፡፡

   ሐ. በዚህ ድንጋጌ በተራ ቁጥር ‹ሀ› እና ‹ለ› የተመለከቱት ምክንያቶች ተደራርበው በተገኙ ጊዜ፣ እያንዳንዱ የሚያስጨምረው እርከን ተደምሮ የሚያስገኘው እርከን ድረስ ከፍ ይላል፡፡ ይሁንና በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል ለወንጀሉ ከተቀመጠው የቅጣት ጣሪያ በላይ አይሄድም፡

5. ለወንጀል ሕጉ አንቀጽ 669 (ከባድ ስርቆት) ለአንቀጽ 665 የተዘጋጀውን የገንዘብ መጠን መነሻ መሰረት ባደረገ ሜልኩ እና በድንጋጌው የተመለከቱትን ማክበጃዎች ማለትም ‹የተሰረቀው እቃ አይነት›፣ ‹ድርጊቱን የፈጸመው አድራጊ ማንነት›፣ ‹የወንጀል አፈጻጸሙ› መሰረት ባደረገ ሜልኩ ዘጠኝ የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

6. ለዚህ መሟያ አፈጻጸም በአንቀጽ 669 የተመለከቱት ሶስቱ ማክበጃ ምክንያቶች የቅጣት ማክበጃ የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸዋል፡፡

7. በአንቀጽ 669 ወንጀሉን የሚያከብዱ ምክንያቶች ከአንድ በላይ ተደራርበው በሚገኙበት ጊዜ የወንጀል ደረጃውንና መነሻ ቅጣቱ ከፍ እንዲል ተደርጓል፡፡ (አባሪ ሶስትን ይመልከቱ)

## አንቀጽ 11. የወንብድና ወንጀሎች(670 እና 671)

[4] በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 662 አነስተኛ ለሆኑ በንብረት መብት ላይ ለሚፈጸሙ ወንጀሎች በደንብ መተላለፍ እንደሚቀጣ የደነገገ ስለሆነ፣ በደንብ መተላለፍ የሚያስቀጣውን ልዩነት ለመፍጠር በሚል የተካተተ ነው፡፡

1. በዚህ መመሪያ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 670 እና 671 ተከሰው ጥፋተኝነታቸው በፍርድ ቤት በተረጋገጠባቸው ወንጀል አድራጊዎች ላይ ቅጣት የሚወሰነው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት ነው፡፡

2. የወንብድና ወንጀል እንደስርቆትና ሙስና ወንጀል የማይገባ ጥቅምን ለማግኘት የሚፈጸም ወንጀል በመሆኑ በወንጀሉ የተገኘው ጥቅም ወይም የደረሰው ጉዳትን መጠን መሰረት በማድረግ፣ እንዲሁም የወንብድና ወንጀል ከስርቆት ወንጀል የሚለየው ሀይልን በመጠቀም በመሆኑ፣

    ሀ. የተገኘውን የገንዘብ ጥቅም ወይም የደረሰ ጉዳት እና

    ለ. የሀይል አጠቃቀሙን መሰረት ባደረገ መልኩ

ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 670 በቁጥር ዘጠኝ፣ ለአንቀጽ 671(1) በቁጥር ዘጠኝ፣ እንዲሁም ለ671(2) ሁለት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅቷል፡፡ (አባሪ ሶስትን ይመልከቱ)

3. በዚህ ድንጋጌ ንኡስ አንቀጽ 2 (ለ) እንደተመለከተው የሀይል አጠቃቀምን በተመለከተ ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ደረጃ የወጣላቸው ሲሆን እነርሱም የማስፈራራቱና ሀይል የመጠቀሙ ተግባር የተፈጸመው፣

    ሀ. መሳሪያ ሳይያዝ በሆነ ጊዜ፣ (ዝቅተኛ)

    ለ. መሳሪያ ተይዞ ከሆነ (መካከለኛ)

    ሐ. የጦር መሳሪያ በመያዝ ከሆነ (ከፍተኛ) በማለት

እንደቅደም ተከተላቸው የወንጀል አፈጻጸሙን የሚያከብዱ እንደሚሆኑ ታሳቢ በማድረግ የወንጀል ደረጃዎቹ ተዘጋጅተዋል፡፡

4. በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 671(1) ቅጣቱን ለማክበድ የተካተተው ለዚህ ሲባል በተቋቋመ የወንበዴ ቡድን አባል መሆንን ያካተተ ስለሆነ፣ በዚህ መሰረት የወንበዴ ቡድን አባል ቅጣትን የሚያከብድ በሚሆን መልኩ የወንጀል ደረጃዎችን ለማዘጋጀት ስራ ላይ ውሏል፡፡

## አንቀጽ 12. የሙስና ወንጀሎች(692 እና 693)

1. በዚህ መመሪያ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 692 እና 693 ተከሰው ጥፋተኝነታቸው በፍርድ ቤት በተረጋገጠባቸው ወንጀል አድራጊዎች ላይ ቅጣት የሚወሰነው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ድንጋጌዎች ማለት ነው፡፡

2. የማታለል ወንጀል (አንቀጽ 692) በተመለከተ በወንጀሉ የተገኘው የገንዘቡ ወይም ንብረቱ ጥቅም ግምትን መሰረት በማድረግ የጥቅሙ መጨመር ታሳቢ ባደረገ መልኩ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ሰባት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ (አባሪ ሶስትን ይመልከቱ)

3. በወንጀሉ የተገኘው የጥቅም መጠን እስከ ብር 100 የሆነው በደንብ መተላለፍ የሚታይ ስለሚሆን በአንቀጽ 692 መሰረት የሚከተት አይሆንም፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ሁለት የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣

   ሀ. ወንጀሉ የተፈጸመበት ሰው ወይም ድርጅት በማታለሉ ተግባር በተወሰደበት ንብረት ምክንያት የእለት ኑሮው ወይም የድርጅቱ ስራ አደጋ ላይ የወደቀ ከሆነ የገንዘብ መጠኑን መሰረት አድርጎ ከተመደበበት የቅጣት እርከን በሁለት እርከን ወደላይ ያድጋል፡፡

   ለ. የተወሰደው ንብረት ለምሳሌ ፈንጂ፣ ተቀጣጣይ ወዘተ ከሆነ የገንዘብ መጠኑን መሰረት አድርጎ ከተመደበበት የቅጣት እርከን በሁለት እርከን ወደላይ ያድጋል፡፡

   ሐ. የተወሰደው ንብረት ለወንጀል ተጎጂው ልዩ ትርጉም ያለው ከሆነና ወንጀል አድራጊውም ይህንን እያወቀ የወሰደው ከሆነ በአንድ እርከን ወደላይ ያድጋል፡፡

   መ. በዚህ ድንጋጌ በ‹ሀ›፣ ‹ለ› እና ‹ሐ› የተመለከቱት ምክንያቶች 3 ያሉት ምክንያቶች ተደራርበው በተገኙ ጊዜ፣ እያንዳንዱ የሚያስጨምረው እርከን ተደምሮ የሚያስገኘው እርከን ድረስ ከፍ ይላል፡፡ ይሁንና በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል ለወንጀሉ ከተቀመጠው የቅጣት ጣሪያ በላይ አይሄድም፡፡

5. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 693 ‹የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት› ወንጀል በተመለከተ የገንዘቡን መጠን መሰረት በማድረግ የጥቅሙ መጨመር ታሳቢ ባደረገ መልኩ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ሰባት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ (አባሪ ሶስትን ይመልከቱ)

6. ይሁንና በአንቀጽ 693 መሰረት ወንጀሉ የተፈጸመበት ሰው ወይም ድርጅት በወንጀሉ ምክንያት የእለት ኑሮው ወይም የድርጅቱ ስራ አደጋ ላይ የወደቀ ከሆነ የገንዘብ መጠኑን መሰረት አድርጎ ከተመደበበት የቅጣት እርከን በሁለት እርከን ወደላይ ያድጋል፡፡

# ንኡስ ክፍል ሁለት

## ደረጃ ላልወጣላቸው ወንጀሎች በቅጣት ማንዋሉ መሰረት ስለሚከራበት ሁኔታ

### አንቀጽ 13. ደረጃ ያልወጣላቸውን ወንጀሎች የወንጀል ደረጃና የቅጣት መነሻ እርከን አወሳሰን፣

1. ወደፊት በወንጀል ሕጉ እና በሌሎች የወንጀል ሕጎች ለተደነገጉት ዝርዝር የወንጀል ድርጊቶች የወንጀል ደረጃዎች እየተለየ የሚወጣላቸው ሆኖ፣ ደረጃ ወጥቶ እስከሚጸድብ ድረስ ፍርድ ቤቱ ከዚህ በታች በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት ቅጣት ይወስናል፡፡
2. ወንጀል ሚጸሙ በፍርድ ቤት ተረጋግጦ ወንጀለኛ መሆናቸው የተረጋገጠውን በወንጀል ድንጋጌው ከተቀመጠው መስፈርት(ፍሬነገር) አንጻር እና የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶችን ታሳቢ ከማድረጉ በፊት ወንጀሉን በክብደቱና በአፈጻጸሙ
    ሀ. ዝቅተኛ፣
    ለ. መካከለኛ፣
    ለ. ከባድ የወንጀል ደረጃ በማለት ይመድባል፡፡
3. ፍርድ ቤቱ ወንጀሉን ‹ዝቅተኛ› ‹መካከለኛ› ወይም ‹ከባድ› በማለት ለመመደብ ምክንያቱን በወሳኔ ሰነዱ ላይ ያስቀምጣል፡፡
4. ለወንጀሉ በወጣው ደረጃ መሰረት የቅጣት እርከኑን ለመወሰን እንዲቻል በልዩ ክፍሉ ለወንጀሉ በተቀመጠው የቅጣት መነሻና መድረሻ መካከል ያለውን ርዝመት ለአራት እኩል በመክፈል፣
    ሀ. በወንጀል ሕጉ ለቅጣቱ መነሻ ተብሎ ከተቀመጠው የቅጣት ማጠን የሚጀምረው አንድ አራተኛ (ጊዜ ወይም ማጠን) እርከን አንድ ይባላል፡፡
    ለ. ከመጀመሪያው አንድ አራተኛ ቀጥሎ ያሉት እርከኖች እንደቅደም ተከተላቸው እርከን ሁለት፣ እርከን ሶስት፣ እርከን አራት ይባላሉ፡፡[5]
5. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት ‹ዝቅተኛ› በሚለው የወንጀል ደረጃ ወስጥ ለተመደበው ፍርድ ቤቱ በእርከን አንድ ባለው ፍቅድ ስልጣን (range) ወስጥ መነሻ ቅጣቱን ይወስናል፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት ‹መካከለኛ› በሚለው የወንጀል ደረጃ ወስጥ ለተመደበው ፍርድ ቤቱ በእርከን ሁለት ባለው ፍቅድ ስልጣን (range) ወስጥ መነሻ ቅጣቱን ይወስናል፡፡
7. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት ‹ከባድ› በሚለው የወንጀል ደረጃ ወስጥ ለተመደበው ፍርድ ቤቱ በእርከን ሶስት ባለው ፍቅድ ስልጣን (range) ወስጥ መነሻ ቅጣቱን ይወስናል፡፡

---

[5] ለምሳሌ ከአንድ አመት እስከ አስር አመት የሚያስቀጣ ወንጀል ለአራት ሲከፈል 1) እርከን አንድ ከአንድ አመት– ሶስት አመት ከሶስት ወር፣ 2) እርከን ሁለት ከሶስት አመት ከሶስት ወር– አምስት አመት ከስድስት ወር፣ 3) እርከን ሶስት ከአምስት አመት ከስድስት ወር– ሰባት አመት ከዘጠኝ ወር፣ 4) እርከን አራት ከሰባት አመት ከዘጠኝ ወር– አስር አመት ይሆናል፡፡

8. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 5፣ 6 ወይም 7 ማስረት በፍርድ ቤቱ የተወሰነው ማሻሻ ቅጣት በአባሪ አንድ በተያያዘው የቅጣት ሰንጠረዥ እርከን የትኛው እርከን ላይ እንደሚወድቅ በማየት የቅጣት እርከኑ በሰንጠረዡ ማስረት ይለያል፡፡

9. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 5፣6 ወይም 7 ማስረት ያስቀመጠው የቅጣት ማጠን በአባሪ አንድ በተያያዘው የቅጣት ሰንጠረዥ ሁለት ተከታታይ እርከኖች ወስጥ የሚወድቅ ከሆነ፣ በዝቅተኛው እርከን ወስጥ እንዲመደብ ይደረጋል፡፡[6]

10. በዚህ አንቀጽ ማስረት ቅጣታቸው የሚወሰን የወንጀል አይነቶች በመቀጮ የሚያስቀጡ ሲሆኑ በተደነገገ ጊዜ፣ ወይም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 92 ማስረት መቀጮ መጣል የሚያስፈልግ በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቱ በድንጋጌው ወይም በወንጀል ሕጉ ጠቅላላ ክፍል የተቀመጠውን ጣሪያ ማስረት በማድረግ፣ ‹ለከባዱ› በሕጉ እስከተመለከተው ጣሪያ ድረስ፣ ‹መካከለኛ› ለሆነው በሕጉ ከተመለከተው ጣሪያ አንድ ሶስተኛ በመቀነስ የሚደረስበትን ማጠን ጣሪያ በማድረግ፣ እንዲሁም ‹ዝቅተኛ› ለሆነው ከጣሪያው በሁለት ሶስተኛ ዝቅ ብሎ በሚደርስበት ጣሪያ ሳይበልጥ መቀጮውን ይወስናል፡፡[7]

# ክፍል አራት

## የቅጣት ማክበጃና ማቅለያዎችን ማከላትን በተመለከተ፣

## ንኡስ ክፍል አንድ

## የቅጣት ማክበጃዎችን ማከላትን በተመለከተ፣

### አንቀጽ 14. ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች በሚኖሩበት ቅጣቱ ስለሚከብደበት አሰራር፣

1. ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም በወንጀል ህጉ አንቀጽ 84 ንኡስ አንቀጽ 1 ከ‹ሀ› እስከ ‹ሠ› በአምስት ንኡሳን ድንጋጌዎች ተዘርዝረው የተመለከቱት ማክበጃ ምክንያቶች እያንዳንዳቸው እንደአንድ ማክበጃ ምክንያት በጠቅላላው እንደአምስት የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ተደርገው ተወስደዋል፡፡

---

[6] ለምሳሌ በፍርድ ቤቱ የተጣለው ቅጣት 2 አመት ከ5 ወር ቢሆን ይህ በቅጣት እርከን 12 እና 13 ወስጥ የሚወድቅ ይሆናል፡፡ ስለሆነም ፍርድ ቤቱ በዝቅተኛው ማትም በቅጣት እርከን 12 ወስጥ ይመድበዋል ማለት ነው፡፡

[7] ለምሳሌ የመቀጮው ጣሪያ 10000 ብር ቢሆን፣ ለከባዱ እስከ ብር 10000 ድረስ መቀጮ ይጥላል፡፡ ለመካከለኛው የ10000 አንድ ሶስተኛ ሲቀነስ 6600 ብር ስለሚሆን ከዚህ ጣሪያ ሳይበልጥ መቀጮ ይጥላል፡፡ ዝቅተኛ ለተባለው ሁለት ሶስተኛ ሲቀነስ 3300 ስለሚሆን ከዚህ ጣሪያ ሳይበልጥ መቀጮ ይጥላል ማለት ነው፡፡

2. በእያንዳንዱ ድንጋጌ ‹ሀ›፣‹ለ›፣‹ሐ›፣‹መ›፣‹ሠ› ከተመለከቱት ምክንያቶች አንዱ እንኳን ተሟልቶ ቢገኝ አንድ የቅጣት ማክበጃ እንደተሟላ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡[8]

3. በእያንዳንዱ ድንጋጌ ‹ሀ›፣‹ለ›፣‹ሐ›፣‹መ›፣‹ሠ› ከተመለከቱት ምክንያቶች አንዱ ወይም በከፊል ወይም በሙሉ ተሟልተው ሲገኙ፣ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱ ሲከብድ የሚደርስበት የቅጣት እርከን ወሰጥ ባለው ፍቅድ ስልጣን (range) ከዝቅተኛው እስከ ጣሪያው ባለው ወሰጥ ቅጣቱ የሚወድቅበትን ይወስናል፡፡

4. ፍርድ ቤቱ ለእያንዳንዱ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት መነሻ ቅጣቱ ከሚያርፍበት የቅጣት እርከን አንድ እርከን ወደላይ ይጨምራል፡፡ ስለሆነም በቅጣት ማክበጃዎቹ ቁጥር ልክ የቅጣት እርከኑም እንደዚሁ ያድጋል፡፡ ይሁንና በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል ለወንጀሉ ከተቀመጠው የቅጣት ጣሪያ ማለፍ አይችልም፡፡

## አንቀጽ 15. ልዩ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች በሚኖሩ ጊዜ ቅጣቱ ስለሚከብድበት አሰራር፣

1. ወንጀል አድራጊው በተደራራቢ ወንጀሎች ጥፋተኛ መሆኑ የተረጋገጠ በሆነ ጊዜ፣

   ሀ. በወንጀል ሕጉ 184 በተመለከተው መሰረት ለእያንዳንዱ ወንጀል ቅጣት ወስኖ የሚደመር በሆነ ጊዜ በዚህ መመሪያ መሰረት ለእያንዳንዱ ወንጀል መነሻ ቅጣት ካስቀመጠ በኋላ እነዚህን በመደመር ድምሩ የቅጣት መጠን የሚያርፍበትን ዝቅተኛ የቅጣት እርከን በመምረጥ እርከኑን ይለያል፡፡ በመቀጠልም በህጉ ከተመለከተው ጠቅላላ ጣሪያ ሳይበልጥ ጠቅላላ ማክበጃ ምክንያቶችን መሰረት በማድረግ ቅጣቱን በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 በተመለከተው መሰረት ያሳድጋል፡፡

   ለ. በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 187 ንኡስ አንቀጽ 1 ሁለተኛ ፓራግራፍ እና ንኡስ አንቀጽ 2(ለ) እንደተመለከተው ቅጣቱ የሚከብድ በሆነ ጊዜ ለእያንዳንዱ ተደራራቢ ወንጀል ከመነሻው እርከን በሁለት እርከን እንዲያድግ ያደርጋል፡፡ በመቀጠልም ጠቅላላ ቅጣት ማክበጃ ምክንያቶችን መሰረት አድርጎ ያከብዳል፡፡ ይሁንና ለከባዱ ወንጀል ከተደነገገው ጣሪያ መብለጥ የለበትም፡፡

2. ጥፋተኛው ደጋጋሚ ወንጀለኛ በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ለአዲሱ ወንጀል የመነሻ ቅጣቱ የሚያርፍበትን እርከን በዚህ መመሪያ መሰረት ከለየ በኋላ ቅጣቱን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 188 በተመለከተው መሰረት ከአንድ እርከን ጀምሮ ቅጣቱን ሊያሳድግ ይችላል፡፡ በመቀጠልም ጠቅላላ ቅጣት ማክበጃ ምክንያቶችን መሰረት በማድረግ ቅጣቱን ያከብዳል፡፡

---

[8] ለምሳሌ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 84(1)(ሀ) ከተመለከቱት ማክበጃዎች አንዱን ለምሳሌ በስግብግብነት ያደረገ መሆኑ ከተረጋገጠ አንድ ማክበጃ ምክንያት እንደተሟላ ይቆጠራል፡፡

# ንኡስ ክፍል ሁለት

# የቅጣት ማቅለያዎችን ማስላትን በተመለከተ፤

## አንቀጽ 16. ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች በሚኖሩበት ጊዜ ስለሚኖረው አሰራር፤

ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያዎች በሚኖሩ ጊዜ ቅጣቱ የሚቀለው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከተው መሰረት ይሆናል፡፡

1. ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም በወንጀል ህጉ አንቀጽ 82 ንኡስ አንቀጽ 1 ከ‹ሀ› እስከ ‹ሠ› በአምስት ንኡሳን ድንጋጌዎች ተዘርዝረው የተመለከቱት ማቅለያ ምክንያቶች እያንዳንዳቸው እንደአንድ ማቅለያ ምክንያት በጠቅላላው እንደአምስት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ተደርገው ተወስደዋል፡፡

2. በእያንዳንዱ ድንጋጌ ‹ሀ›፣‹ለ›፣‹ሐ›፣‹መ›፣‹ሠ› ከተመለከቱት ምክንያቶች አንዱ እንኳን ተሟልቶ ቢገኝ አንድ የቅጣት ማቅለያ እንደተሟላ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

3. በእያንዳንዱ ድንጋጌ ‹ሀ›፣‹ለ›፣‹ሐ›፣‹መ›፣‹ሠ› ከተመለከቱት ምክንያቶች አንዱ ወይም በከፊል ወይም በሙሉ ተሟልተው ሲገኙ፣ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱ ሲቀል የሚደርስበት የቅጣት እርከን ወስጥ ባለው ፍቅድ ስልጣን (range) ከዝቅተኛው እስከ ጣሪያው ባለው ወስጥ ቅጣቱ የሚወድቅበትን ይወስናል፡፡

4. በቀላል እስራት ለሚያስቀጡ ወንጀሎች ፍርድ ቤቱ ለእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት መነሻ ቅጣቱ ከሚያርፍበት የቅጣት እርከን አንድ እርከን ወደታች ይቀንሳል፡፡ ስለሆነም በቅጣት ማቅለያዎቹ ቁጥር ልክ የቅጣት እርከኑም እንደዚሁ ይቀንሳል፡፡ ይሁንና በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 179 ከተደነገገው ዝቅተኛ ወለል በታች ሊወርድ አይችልም፡፡

5. የቅጣት መነሻው 1 አመት ጽኑ እስራት በሆነ ወንጀሎች ጥፋተኛ ሆነው የተገኙ በእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ በሁለት እርከን ይቀንሳል፡፡ ይሁንና በወንጀል ህጉ ከተመለከተው 6 ወር ጽኑ እስራት በታች ቅጣቱ አይወርድም፡፡

6. የቅጣት መነሻቸው ከአንድ አመት በላይ እና ከሰባት አመት በታች በጽኑ እስራት በሚያስቀጡ ወንጀሎች ጥፋተኛ ሆነው የተገኙ በእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ሁለት እርከን ይቀነሳል፡፡ ይሁንና ቅጣቱ ሲቀል በወንጀል ሕጉ ከተደነገገው ዝቅተኛ 1 አመት በታች አይወርድም፡፡

7. የቅጣት ማኣሻቸው ሰባት አመትና ከሰባት አመት በላይ ለሆኑ ወንጀሎች በእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ሶስት እርከን ይቀነሳል፡፡ ይሁንና ቅጣቱ ሲቀል ከጠቅላላው ዝቅተኛ 1 አመት በታች አይወርድም፡፡

8. የቅጣት ማኣሻቸው እድሜ ልክ ጽኑ እስራት ለሆኑ ወንጀሎች በእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ሶስት እርከን ይቀነሳል፡፡ ይሁንና ቅጣቱ ሲቀል ከአስር አመት በታች አይወርድም፡፡

9. የቅጣት ማኣሻቸው የሞት ቅጣት ለሆኑ ወንጀለኞች በእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት አራት እርከን ይቀነሳል፡፡ ይሁንና ቅጣቱ ሲቀል ከሃያ አመት በታች አይሆንም፡፡

## አንቀጽ 17. ልዩ የቅጣት ማቅለያዎች

በወንጀል ሕጉ ቅጣትን በማሰለው እንዲያቀል በፈቀደ ጊዜ ፍርድ ቤቱ በዚህ መመሪያ በተማለከተው ማሰረት ሳይወሰን ቅጣቱን በማቅለል ይወስናል፡፡

## አንቀጽ 18. በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 86 ማሰረት የቅጣት ማክበጃና ማቅለያዎች በሚኖሩ ጊዜ ስለሚኣላበት ሁኔታ

ፍርድ ቤቱ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 86 ማሰረት ቅጣቱን ማቅለያ ወይም ማክበጃ ምክንያቶች የሚጠቀም በሆነ ጊዜ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 ጠቅላላ ማክበጃ ምክንያቶች እና አንቀጽ 16 ጠቅላላ ማቅለያ ምክንያቶች በሚኖሩ ጊዜ እንደሚኖረው አሰራር ቅጣቱን በማክበድ ወይም በማቅለል ይወስናል፡፡

# ክፍል አምስት

# የቅጣት አሰላል ስነስርአት በሚማለከት

## አንቀጽ 19. የቅጣት አሰላል ስነስርአት ቅደም ተከተል.

በዚህ መመሪያ ማሰረት ፍርድ ቤቱ ቅጣት ሲወስን የሚከተለዉን ቅደም ተከተል ማሰረት በማድረግ ይሆናል፡፡

1. የወንጀል ደረጃ ደረጃ የወጣለቸዉን የወንጀል አይነቶች በተማለከተ፣

   ሀ. የጥፋተኝነት ዉሳኔ ከተሰጠ በኋላ በዚህ መመሪያ በክፍል ሶስት በተማለከተው ማሰረት የወንጀሉ ደረጃን ይወስናል፡፡

   ለ. በመቀጠልም የወንጀሉ ደረጃ የሚወድቅበትን የቅጣት እርከን በአባሪ አንድ ከተያያዘው የቅጣት ሰንጠረዥ ላይ ይለያል፡፡

ሐ. በመቀጠልም በእርከኑ በተቀመጠው የቅጣት መነሻና መድረሻ መካከል ባለው ፍቅድ ስልጣን (range) ወስጥ መነሻ ቅጣት ይወስናል፡፡

መ. በማክረጃ የተረጋገጡ ልዩ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ካሉ በዚህ መመሪያ መሰረት ቅጣቱን አክብዶ ቅጣቱ የሚደርስበትን እርከን በማስቀመጥ ቅጣቱን ይወስናል፡፡

ሠ. በመቀጠል በማክረጃ በተረጋገጡ ጠቅላላ ማክበጃ ምክንያቶች መሰረት እርከኑን በመጨመር ቅጣቱን ይወስናል፡፡

ረ. በማክረጃ በተረጋገጡ ማቅለያ ምክንያቶች መሰረት የሚቀነሰውን እርከን በማየት ወርዶ እርከኑ የሚያርፍበትን በማየት ቅጣቱን ይወስናል፡፡

ሰ. የሚጣለው የእስራት ቅጣት እስከ ስድስት ወር ወይም ከስድስት ወር በታች በሚሆንበት ጊዜ በዚህ መመሪያ ተያይዞ በሚገኘው የቅጣት እርከን ሰንጠረዥ መሰረት በግዴታ ስራ እንዲለወጥ ሊወስን ይችላል፡፡

ሸ. በቅጣት ማቅለያ ጊዜ የእስራት ቅጣትን ወደ መቀጮ መቀየር እንደሚቻል በህጉ በተደነገገው መሰረት ወደመቀጮ ሲቀየርም በዚህ መመሪያ መሰረት ይሆናል፡፡

2. የወንጀል ደረጃ ያልወጣላቸውን የወንጀል አይነቶች በተመለከተ፣

ሀ. የጥፋተኝነት ወሳኔ ከተሰጠ በኋላ በድንጋጌው ከተቀመጠው አንጻር የወንጀሉ ከባድነትን በተመለከተ ‹ዝቅተኛ› ወይም ‹መካከለኛ› ወይም ‹ከባድ› በማለት በቅድሚያ ይለያል፡፡

ለ. በዚህ መመሪያ በተመለከተው መሰረት መነሻ ቅጣቱ የሚወድቅበትን እርከን ይለያል፡፡

ሐ. ከዚህ በመቀጠል በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ከንኡስ አንቀጽ ሙሸ በተመለከተው መሰረት ስሌቱን በማስራት ቅጣቱን ይወስናል፡፡

# ክፍል ስድስት
# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## አንቀጽ 20. ወንጀሉ በመካራ ደረጃ የቀረ ከሆነ፣ ወንጀሉን በማነሳሳት ወይም በአባሪነት የሰራ በሆነ ጊዜ፣

ወንጀሉ ሳይፈጸም በመካራ ደረጃ የቀረ ሲሆን፣ ወይም ወንጀል አድራጊው በማነሳሳትና በአባሪነት ጥፋተኛ ተብሎ የተወሰነ በሆነ ጊዜ ቅጣት አወሳሰንን በተመለከተ ለተፈጸመው ወንጀል በህጉ ከተደነገገው ቅጣት

በሁለት እርከን ዝቅ በማድረግ የቅጣቱ መነሻ ይሆናል፡፡ ይሁንና ለወንጀሉ በልዩ ክፍሉ ከተመለከተው መነሻ ቅጣት ዝቅ ሊል አይችልም፡፡

## አንቀጽ 21. በዚህ ማንዋል የተመለከቱት መለጮዎች ቅጣት ሊወሰንበት የቀረበውን የወንጀል አይነት የማይወክሉ ሆነው በተገኙበት ጊዜ

1. ፍርድ ቤቱ የወንጀል አፈጻጸሙም ሆነ ባህርይው በዚህ መመሪያ ደረጃ በወጣላቸው ሊወክል የማይችል ሆኖ ባገኘው ጊዜ ወይም በዚህ መመሪያ በተቀመጠው መሰረት ቅጣቱን መወሰን ፍትህ የሚዛባ ነው ብሎ ያመነ ከሆነ፣ የዚህን የቅጣት መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ የማይችልበትን ምክንያት በዝርዝር በማስቀመጥ በዚህ መመሪያ ከተቀመጠው በተለየ ሜሌኩ ቅጣት ሊወስን ይችላል፡፡ ይሁንና ይህ በልዩ ሁኔታ በጣም አስፈላጊ እና ፍትህ በእርግጥም ይዛባል ተብሎ ሲታመን ብቻ ሊፈጸም የሚገባ ነው፡፡

2. ፍርድ ቤቱ በዚህ እንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 በተደነገገው መሰረት መመሪያው ከሚያስቀምጠው በተለየ እርከን ላይ እንዲያርፍ በማድረግ በሚወስንበት ጊዜ ሁሉ፣ ይህንኑ ለሚመለከተው አካል ማስታወቅ ወይም ሚጃወን ማስተላለፍ ይኖርበታል፡፡

## አንቀጽ 22. የንብረት ግምትን መወሰንን በተመለከተ

1. ወንጀሉ የተፈጸመው በውጭ ገንዘብ ላይ ከሆነ፣ የገንዘቡ ምንዛሪ ማጠን ቅጣቱ ሊወሰን ባለበት ጊዜ ባለው ምንዛሪ መሰረት ይሆናል፡፡

2. በወንጀሉ የተወሰደው ንብረት በሚያንበት ጊዜ የንብረቱን ግምት በተመለከተ ተከሳሹ ክርክር ካቀረበ እና የተከሳሹ ክርክር ተቀባይነት ቢያገኝ የቅጣት እርከኑን የሚቀየር ከሆነ እና በፍርድ ቤቱ እምነት በአቃቤ ህግ የቀረበው ግምት ምክንያታዊ ያልሆነና ፍትህን ያዛባል ብሎ ሲያምን የራሱን ግምት በማስቀመጥ የወንጀል ደረጃውንና የቅጣት እርከኑን ይወ1ስናል፡፡

## አንቀጽ 23. አቃቤ ሕግ እና ተከሳሾች የቅጣት አስተያየት በዚህ መመሪያ መሰረት እንዲያቀርቡ ስለማድረግ፣

1. ፍርድ ቤቶች አቃቤ ሕጎችም ሆኑ ጥፋተኞች የቅጣት ወሳኔ አስተያየት በሚያቀርቡ ጊዜ በዚህ መመሪያ መሰረት መሆኑን ያረጋግጣሉ፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 በተመለከተው መሰረት እንዲፈጸም ፍርድ ቤቶች አቃቤሕጎችም ሆኑ ተከሳሾች ስለመመሪያው እንዲያወቁ ያደርጋሉ፡፡ በተለይም በጠበቃ ለሚወከሉ ተከሳሾች በመመሪያው መሰረት የቅጣት አስተያየት በማስረጃ አስደግፈው ማቅረብ እንዳለባቸው ይገልጹላቸዋል፡፡

## አንቀጽ 24. ይህንን መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ በየፍርድ ቤቱ ሊሰሩ የሚገባቸው ተግባራቶች

ማንኛውም ፍርድ ቤት ይህ መመሪያ ከሚያስቀምጠው የቅጣት አወሳሰን ወጪ ተወስነው የሚገኙ ጉዳዮችን ዝርዝር በየጊዜው እያዘጋጀ ለጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ያስታውቃል፡፡

## አንቀጽ 25. መመሪያው ስራ ላይ የሚውልበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ------- ቀን ጀምሮ ስራ ላይ ይውላል፡፡

አባሪዎች

1. (አባሪ አንድ) ነጻነትን የሚያሳጡ ቅጣቶች እርከን ሰንጠረዥ
2. (አባሪ ሁለት) የገንዘብ መቀጮ የሚያሳይ እርከን ሰንጠረዥ
3. (አባሪ ሶስት) የወንጀል ደረጃዎችና የቅጣት እርከን የሚያሳይ ሰንጠረዥ

## አባሪ አንድ

## ነጻነትን የሚያሳጡ የቅጣት እርከኖች ሰንጠረዥ

| | | |
|---|---|---|
| እርከን 1 | ከ1 ቀን-20 ቀን የግዴታ ስራ | ከ1 ብር- 100 ብር |
| እርከን 2 | ከ10 ቀን-3 ወር እስራት ወይም<br>ከ10 ቀን-3 ወር የግዴታ ስራ | እስከ ብር - 500 ብር |
| እርከን 3 | ከ2 ወር - 5 ወር ወይም<br>ከ2 ወር-3 ወር የግዴታ ስራ | እስከ ብር- 800 ብር |
| እርከን 4 | ከ4 ወር- 7 ወር | እስከ ብር 1000 |
| እርከን 5 | ከ6 ወር-9 ወር | እስከ ብር 1500 |
| እርከን 6 | ከ8 ወር-1 አመት | እስከ ብር 2000 |
| እርከን 7 | ከ1 አመት-1 አመት ከ3 ወር | ከዚህ ጀምሮ ሬንጁን ለመወሰን ጣሪያው ከጫሻው በ25 በመቶ እንዲያደግ ተደርጓል፡፡ |
| እርከን 8 | ከ1 አመት ከ2 ወር-1 አመት ከ6 ወር | |

| | | |
|---|---|---|
| እርከን 9 | ከ1 አመት ከ4 ወር -1 አመት ከ8 ወር | |
| እርከን 10 | ከ1 አመት ከ6 ወር-1 አመት ከ10 ወር | |
| እርከን 11 | ከ1 አመት ከ8 ወር-2 አመት ከ2 ወር | |
| እርከን 12 | ከ2 አመት - 2 አመት ከ6 ወር | |
| እርከን 13 | ከ2 አመት ከ3 ወር-2 አመት ከ9 ወር | ከዚህ ጀምሮ ሬንጁ በስድስት ወር ወስጥ እንዲቆይ ተደርጓል፡፡ |
| እርከን 14 | ከ2 አመት ከ6 ወር-3 አመት | |
| እርከን 15 | ከ2 አመት ከ9 ወር-3 አመት ከ3 ወር | |
| እርከን 16 | ከ3 አመት - 3 አመት ከ7 ወር | ከዚህ ጀምሮ ሬንጁ በ20 በመቶ እያደገ እንዲሄድ ተደርጓል፡ |
| እርከን 17 | ከ3 አመት ከ3 ወር-3 አመት ከ11 ወር | |
| እርከን 18 | ከ3 አመት ከ7 ወር- 4 አመት ከ4 ወር | |
| እርከን 19 | ከ4 አመት- ከ4 ወር ከ10 ወር | |
| እርከን 20 | ከ4 አመት ከ5 ወር-5 አመት ከ4 ወር | |
| እርከን 21 | ከ5 አመት - 6 አመት | |
| እርከን 22 | ከ5 አመት ከ6 ወር-6 አመት ከ7 ወር | |
| እርከን 23 | ከ6 አመት- 7 አመት ከ2 ወር | |
| እርከን 24 | ከ6 አመት ከ6 ወር- 7 አመት ከ8 ወር | |
| እርከን 25 | ከ7 አመት- 8 አመት ከ4 ወር | |
| እርከን 26 | ከ7 አመት ከ8 ወር- 9 አመት ከ2 ወር | |
| እርከን 27 | ከ8 አመት ከ5 ወር- 10 አመት | |
| እርከን 28 | ከ9 አመት - 10 አመት ከ10 ወር | |

| | | |
|---|---|---|
| እርከን 29 | ከ10 አመት– 12 አመት | |
| እርከን 30 | ከ11 አመት– 13 አመት ከ2 ወር | |
| እርከን 31 | ከ12 አመት– 14 አመት ከ5 ወር | |
| እርከን 32 | ከ13 አመት– 15 አመት ከ8 ወር | |
| እርከን 33 | ከ14 አመት– 16 አመት ከ10 ወር | |
| እርከን 34 | ከ15 አመት – 18 አመት | |
| እርከን 35 | ከ16 አመት ከ6 ወር – 19 አመት ከ 6 ወር | |
| እርከን 36 | ከ18 አመት – 21 አመት ከ8 ወር | |
| እርከን 37 | ከ20 አመት – 25 አመት | |
| እርከን 38 | ከእድሜ ልክ እስራት– የሞት ቅጣት | |
| እርከን 39 | የሞት ቅጣት | |

| አባሪ ሁለት<br><br>**<u>የገንዘብ መቀጫ የሚሟለከት ሰንጠረዥ</u>** | | |
|---|---|---|
| የመቀጮ እርከን | የገንዘብ መቀጮው ጣሪያ | |
| እርከን 1 | እስከ 1000 | |
| እርከን 2 | እስከ 2000 | |
| እርከን 3 | እስከ 3000 | |
| እርከን 4 | እስከ 5000 | |
| እርከን 5 | እስከ 7000 | |
| እርከን 6 | እስከ 10000 | |
| እርከን 7 | እስከ 20000 | |
| እርከን 8 | እስከ 30000 | |
| እርከን 9 | እስከ 40000 | |
| እርከን 10 | እስከ 50000 | |
| እርከን 11 | እስከ 75000 | |
| እርከን 12 | እስከ 100000 | |
| እርከን 13 | እስከ 125000 | |

| | | |
|---|---|---|
| እርከን 14 | እስከ 150000 | |
| እርከን 15 | እስከ 200000 | |
| እርከን 16 | እስከ 250000 | |
| እርከን 17 | እስከ 300000 | |
| እርከን 18 | እስከ 350000 | |
| እርከን 19 | እስከ 400000 | |
| እርከን 20 | እስከ 500000 | |

# አባሪ ሶስት

## የወንጀል ደረጃዎች እና ማሻ የቅጣት እርከን

| የወንጀል ህጉ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ ማግለጫ | የእስራት ቅጣት ማሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ ማሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| **በስልጣን አለአግባብ ማልገል** | | | | |
| 407(1) | | | | |
| | ደረጃ 1 | ዝቅተኛ ስልጣን፣ ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ በችግር፣ | 7 | 2 |
| | ደረጃ 2 | ዝቅተኛ ስልጣን፣ ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ ከባድ አላሜ | 10 | 3 |
| | ደረጃ 3 | 3. ዝቅተኛ ስልጣን፣ መካከለኛ ጥቅም/ጉዳት/ በችግር፣ ወይም<br>4. መካከለኛ ስልጣን፣ ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ በችግር፣ | 13 | 4 |
| | ደረጃ 4 | 1. ዝቅተኛ ስልጣን፣ መካከለኛ ጥቅም/ጉዳት፣ ከባድ አላሜ ወይም<br>2. መካከለኛ ስልጣን፣ ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ ከባድ አላሜ | 16 | 5 |
| | ደረጃ 5 | መካከለኛ ስልጣን፣ መካከለኛ ጥቅም/ጉዳት/በችግር፣ | 19 | 6 |
| | ደረጃ 6 | መካከለኛ ስልጣን፣ መካከለኛ ጥቅም/ጉዳት፣ ከባድ አላሜ | 23 | 6 |
| 407(2) | | | | |
| | ደረጃ 1 | 1. ከፍተኛ ስልጣን፣ ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ በችግር፣ ወይም<br>2. ዝቅተኛ ስልጣን፣ ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ በችግር፣ | 25 | 7 |
| | ደረጃ 2 | 1. ከፍተኛ ስልጣን፣ ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ ከባድ አላሜ ወይም<br>2. ዝቅተኛ ስልጣን፣ ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ ከባድ አላሜ | 26 | 8 |

| የወንጀል ህጉ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | **የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ** | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| | ደረጃ 3 | 1. ከፍተኛ ስልጣን፣ መካከለኛ ጥቅም/ጉዳት፣ በችግር፣<br>2. መካከለኛ ስልጣን፣ ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ በችግር፣ | 27 | 9 |
| | ደረጃ 4 | 1. ከፍተኛ ስልጣን፣ መካከለኛ ጥቅም/ጉዳት፣ ከባድ አላማ<br>2. መካከለኛ ስልጣን፣ ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ ከባድ አላማ | 28 | 10 |
| 407(3) | | | | |
| | ደረጃ 1 | ከፍተኛ ስልጣን፣ ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ በችግር፣ | 29 | 11 |
| | ደረጃ 2 | ከፍተኛ ስልጣን፣ ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ ከባድ አላማ | 32 | 12 |
| | | **የስርቆት ወንጀሎች** | | |
| 665 | | **ስርቆት** | | |
| | ደረጃ 1 | ከብር 100- 1000 | 2 | |
| | ደረጃ 2 | ከብር 1000-2000 | 4 | |
| | ደረጃ 3 | ከብር2000-4000 | 6 | |
| | ደረጃ 4 | ከብር 4000-10000 | 8 | |
| | ደረጃ 5 | ከብር 10000-50000 | 10 | |
| | ደረጃ 6 | ከብር 50000-100000 | 12 | |
| | ደረጃ 7 | ከብር 100000 በላይ | 14 | |
| 669 | | **ከባድ ስርቆት** | | |
| | ደረጃ 1 | እስከ ብር 1000 ሆኖ በ669 የተመለከተው አንድ ማክበጃ ተሟልቶ ሲገኝ፣ | 7 | |
| | ደረጃ 2 | 1. እስከ ብር 1000 ሆኖ ሁለት ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ ወይም | 9 | |

| የወንጀል ህጉ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| | | 2. እስከ ብር 2000 ሆኖ አንድ ማከበጃ ተሟልቶ ሲገኝ፣ | | |
| | ደረጃ 3 | 1. እስከ 1000 ሆኖ ሶስት ማከበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ ወይም<br>2. እስከ ብር 2000 ሆኖ ሁለት ማከበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ ወይም<br>3. እስከ ብር 4000 ሆኖ አንድ ማከበጃ ተሟልቶ ሲገኝ፣ | 11 | |
| | ደረጃ 4 | 1. እስከ 2000 ሆኖ ሶስቱም ማከበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ ወይም<br>2. እስከ 4000 ሆኖ ሁለት ማከበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ ወይም<br>3. እስከ 10000 ሆኖ አንድ ማከበጃ ተሟልተው ሲገኙ፣ | 13 | |
| | ደረጃ 5 | 1. እስከ ብር 4000 ሆኖ ሶስቱም ማከበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ ወይም<br>2. እስከ ብር 10000 ሆኖ ሁለቱ ማከበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ ወይም<br>3. እስከ 50000 ሆኖ አንድ ማከበጃ ተሟልቶ ሲገኝ፣ | 15 | |
| | ደረጃ 6 | 1. እስከ 10000 ሆኖ ሶስቱም ማከበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ ወይም<br>2. እስከ 50000 ሆኖ ሁለት ማከበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ ወይም<br>3. እስከ 100000 ሆኖ አንድ ማከበጃ ተሟልቶ ሲገኝ፣ | 18 | |
| | ደረጃ 7 | 1. እስከ 50000 ሆኖ ሶስቱም ማከበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ ወይም<br>2. እስከ 100000 ሆኖ ሁለት ማከበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ ወይም | 21 | |

| የወንጀል ህጉ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| | | 3. ከብር 100000 በላይ ሆኖ አንድ ማከበጃ ተሟልቶ ሲገኝ፣ | | |
| | ደረጃ 8 | 1. እስከ 100000 ሆኖ ሶስቱም ማከበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ ወይም<br>2. ከ100000 በላይ ሆኖ ሁለት ማከበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ | 24 | |
| | ደረጃ 9 | ከብር 100000 በላይ ሆኖ ሶስቱም ማከበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ | 27 | |
| **የማታለል ወንጀሎች** | | | | |
| 692 | **አታላይነት** | | | |
| | ደረጃ 1 | ከብር 100 እስከ ብር 1000 | 2 | 1 |
| | ደረጃ 2 | ከብር 1000-2000 | 4 | 1 |
| | ደረጃ 3 | ከብር 2000-4000 | 6 | 2 |
| | ደረጃ 4 | ከብር 4000-10000 | 8 | 3 |
| | ደረጃ 5 | ከብር 10000-50000 | 10 | 3 |
| | ደረጃ 6 | ከብር 50000-100000 | 12 | 4 |
| | ደረጃ 7 | ከብር 100000 በላይ | 14 | 4 |
| 693 | **የሚዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት** | | | |
| 693(1) | | | | |
| | ደረጃ 1 | ከብር 100 እስከ ብር 1000 | 2 | 1 |

| የወንጀል ህጉ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| | ደረጃ 2 | ከብር 1000-2000 | 5 | 1 |
| | ደረጃ 3 | ከብር 2000-4000 | 8 | 2 |
| | ደረጃ 4 | ከብር 4000-10000 | 11 | 3 |
| | ደረጃ 5 | ከብር 10000-50000 | 14 | 4 |
| | ደረጃ 6 | ከብር 50000-100000 | 18 | 5 |
| | ደረጃ 7 | ከብር 100000 በላይ | 22 | 6 |
| 693(2) | | | | |
| | ደረጃ 1 | በቸልተኝነት የተፈጸመ ማታለል | 2 | 2 |
| **የወንብድና ወንጀሎች** | | | | |
| 670 | **ወንብድና** | | | |
| | ደረጃ 1 | ጉዳት የሚያደርሱ መሳሪያዎችን ሳይዝ፣ የገጠመውን ተቃውሞ ለማስወገድ ከባድ ዛቻ እና የማንገላታት ተግባር ወይም የሀይል ተግባር የፈጸመ እንደሆነ እና በወንጀሉ የተገኘው የገንዘብ ጥቅም እስከ ብር 2000 የሆነ እንደሆነ፣ | 7 | |
| | ደረጃ 2 | 1. ጉዳት የሚያደርሱ መሳሪያዎችን በመያዝ የገጠመውን ተቃውሞ ለማስወገድ ከባድ ዛቻ እና የማንገላታት ተግባር ወይም የሀይል ተግባር የፈጸመ እንደሆነ ወይም<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 2000-10000 የሆነ እንደሆነ | 9 | |
| | ደረጃ 3 | 1. የጦር መሳሪያ በመያዝ የገጠመውን ተቃውሞ ለማስወገድ ከባድ ዛቻ እና የማንገላታት ተግባር ወይም የሀይል ተግባር የፈጸመ እንደሆነ፣ ወይም<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 10000-30000 ከሆነ ወይም<br>3. ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ | 11 | |

| የወንጀል ህጉ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| | | ከብር 2000-10000 ከሆነ፣ | | |
| | ደረጃ 4 | 1. ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 30000-100000 ከሆነ ወይም<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 10000-30000 ከሆነ ወይም<br>3. ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 2000-10000 ከሆነ፣ | 13 | |
| | ደረጃ 5 | 1. ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 100000-300000 ከሆነ ወይም፣<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 30000-100000 ከሆነ ወይም፣<br>3. ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 10000-30000 ከሆነ፣ | 15 | |
| | ደረጃ 6 | 1. ድርጊቱ በደረጃ 1 የተፈጸመው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 300000-1000000 ከሆነ ወይም<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 100000-300000 ከሆነ ወይም<br>3. ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 30000-100000 ከሆነ፣ | 18 | |
| | ደረጃ 7 | 1. ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 1 ሚሊዮን በላይ ከሆነ ወይም፣<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 300 ሺህ እስከ 1 ሚሊዮን ብር ከሆነ ወይም፣<br>3. ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 100000-300000 ከሆነ፣ | 21 | |
| | ደረጃ 8 | 1. ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 1 ሚሊዮን በላይ ከሆነ ወይም፣<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 300000-1000000 ከሆነ፣ | 24 | |
| | ደረጃ 9 | ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 1000000 በላይ ከሆነ፣ | 27 | |
| 671(1) | **ከባድ ወንብድና** | | | |

| የወንጀል ህጉ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| | ደረጃ 1 | ጉዳት የሚያደርሱ መሳሪያዎችን ሳይዝ፣ ወንጀሉ በቡድን የተፈጸመ እንደሆነና የገንዘብ ማጡ እስከ ብር 2000 የሚደርስ እንደሆነ፣ | 21 | |
| | ደረጃ 2 | 1. ጉዳት የሚያደርሱ መሳሪያዎችን በመያዝ አገልሀለሁ ብሎ ያስፈራራ፣ ለዚህም የአካል ጉዳት ያደረሰ እንደሆነና የገንዘቡ ማጠን እስከ ብር 2000 የሚደርስ እንደሆነ ወይም፣<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ ማጠን ከብር 2000-10000 የሚደርስ እንደሆነ፣ | 22 | |
| | ደረጃ 3 | 1. የጦር መሳሪያ ይዞ ያስፈራራ ለዚህም አገልሀለሁ ብሎ ያስፈራራ ወይም የአካል ጉዳት ያደረሰ እንደሆነና የገንዘብ ማጡም እስከ ብር 2000 የሆነ እንደሆነ ወይም፣<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ ማጡ ከብር 10000-30000 ከሆነ ወይም፣<br>3. ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ ማጡ ከብር 2000-10000 ከሆነ፣ | 23 | |
| | ደረጃ 4 | 1. ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ ማጡ ከብር 30000-100000 ከሆነ ወይም፣<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ ማጠን ከብር 10000-30000 ከሆነ ወይም፣<br>3. ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ ማጡ ከብር 2000-10000 ከሆነ፣ | 24 | |
| | ደረጃ 5 | 1. ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ ማጡ ከብር 100000-300000 ከሆነ ወይም፣<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ ማጠን ከብር 30000-100000 ከሆነ ወይም፣<br>3. ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ ማጡ ከብር 10000-30000 ከሆነ፣ | 25 | |
| | ደረጃ 6 | 1. ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ ማጡ ከብር 300000-1000000 ከሆነ ወይም፣<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ ማጠን ከብር 100000-300000 ከሆነ ወይም፣ | 26 | |

| የወንጀል ህጉ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት ማነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ ማነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| | | 3. ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ ማጡ ከብር 30000-100000 ከሆነ፣ | | |
| | ደረጃ 7 | 1. ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ ማጡ ከብር 1000000 በላይ ከሆነ ወይም፣ 2. ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ ማጠን ከብር 300000-1000000 ከሆነ ወይም፣ 3. ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ ማጡ ከብር 100000-300000 ከሆነ፣ | 27 | |
| | ደረጃ 8 | 1. ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ ማጠን ከብር 100000 በላይ ከሆነ ወይም፣ 2. ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ ማጡ ከብር 300000-1000000 ከሆነ፣ | 29 | |
| | ደረጃ 9 | ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ ማጠን ከብር 1000000 በላይ ከሆነ፣ | 31 | |
| 671(2) | | | | |
| | ደረጃ 1 | ወንጀል ለመፈፀም ከተደራጀ ቡድን ጋር በመሆን ወይም የጦር መሣሪያ ወይም ሌላ አደገኛ መሣሪያ በመያዝ የሕዝብ ፀጥታን አደጋ ላይ የሚጥል ወይም የተለየ ጨካኝነትን የሚያሳይ ዘዴን የተጠቀመ ወይም የተፈፀመው ተግባር ዘላቂ የአካል ጉዳትን ወይም ሞትን ያስከተለ እንደሆነ፣ | 38 | |
| | ደረጃ 2 | በጦር መሣሪያ አማካይነት በልማደኛነት በቡድን በሚፈፀም ወንብድና የተለየ ጨካኝነትን የሚያሳይ ዘዴ በማጠቀም የተፈፀመው ተግባር ሞትን ያስከተለ እንደሆነ፣ | 39 | |
| በሰው አካል ወይም ጤንነት ላይ ጉዳት ማድረስ | | | | |
| 555 | ታስቦ የሚፈጸም ከባድ የአካል ጉዳት | | | |

| የወንጀል ህጉ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| | ደረጃ 1 | ለድን የማችል የአካል ጉዳት ያደረሰ፣ | 7 | |
| | ደረጃ 2 | 1. አንዱን አካል ያጎደለ ወይም<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ መዋዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣ | 10 | |
| | ደረጃ 3 | 1. አስፈላጊ ብልቱን ያጎደለ፣ በሽታ እንዲይዘው ያደረገ ወይም<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ መዋዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣ | 13 | |
| | ደረጃ 4 | 1. ሜልኩን ያበላሸ ከሆነ ወይም<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ መዋዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣ | 16 | |
| | ደረጃ 5 | 1. በሰውነቱ ወይም በአእምሮው ለዘውትር ጠንቅ ያተረፈ (ሰርቶ መበላት እንዳይችል ያደረገው) ወይም<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 4 የተመለከተው ሆኖ መዋዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣ | 19 | |
| | ደረጃ 6 | 1. የተጎጂውን ህይወት የሚየሰጋ ከሆነ ወይም<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 5 የተመለከተው ሆኖ መዋዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣ | 23 | |
| | ደረጃ 7 | ድርጊቱ በደረጃ 6 የተመለከተው ሆኖ መዋዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣ | 27 | |
| 557[9] | በቁጥር 557 ያለው ማቅለያ ተሟልቶ በሚገኝበት ጊዜ ለ555 የቅጣት እርከኖች በሚከተለው ሜልኩ ይሆናል፡፡ | | | |
| 555 | | | | |

[9] በ557 ያሉት ማቅለያዎች ባሉ ጊዜ ቅጣቱ እንደሚቀል ያስቀምጣል፡፡ ሲቀልም ቅጣቱ ከሁለት አመት ያልበለጠ እንዲሁም ከብር 4000 ያልበለጠ መቀጫ እንደሚሆን ያስቀምጣል፡፡ ስለሆነም በዚህ ድንጋጌ ስር የተቀመጡት የቅጣት ደረጃዎች ታሳቢ ባደረገ ሜልኩ የቅጣት መነሻቸው እንዲስተካከል ተደርጓል፡፡

| የወንጀል ህጉ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | **የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ** | የእስራት ቅጣት ማሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ ማሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| | ደረጃ 1 | ለድን የሚችል የአካል ጉዳት ያደረሰ፣ | 5 | 1 |
| | ደረጃ 2 | 1. አንዱን አካል ያጎደለ ወይም<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ ሞዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣ | 6 | 2 |
| | ደረጃ 3 | 1. አስፈላጊ ብልቱን ያጎደለ፣ በሽታ እንዲይዘው ያደረገ ወይም<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ ሞዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣ | 7 | 2 |
| | ደረጃ 4 | 1. ሜከሁን ያበላሸ ከሆነ ወይም<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ ሞዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣ | 8 | 3 |
| | ደረጃ 5 | 1. በሰውነቱ ወይም በአእምሮው ለዘወትር ጠንቅ ያተረፈ (ሰርቶ መበላት እንዳይችል ያደረገው) ወይም<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 4 የተመለከተው ሆኖ ሞዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣ | 9 | 3 |
| | ደረጃ 6 | 1. የተጎጂውን ህይወት የሚያሰጋ ከሆነ ወይም<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 5 የተመለከተው ሆኖ ሞዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣ | 10 | 4 |
| | ደረጃ 7 | ድርጊቱ በደረጃ 6 የተመለከተው ሆኖ ሞዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣ | 11 | 4 |
| 556 | **ታስቦ የሚፈጸም ቀላል የአካል ጉዳት** | | | |
| | ደረጃ 1 | የደረሰው ጉዳት በ555 ወስጥ የሚወድቅ ቀላል ጉዳት ከሆነ፣ | 2 | 3 |
| | ደረጃ 2 | ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ በድንጋጌው ከተቀመጡት ማክበጃዎች አንዱ ተሟልቶ ከተገኘ፣ | 5 | 4 |

| የወንጀል ህጉ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| | ደረጃ 3 | ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ በድንጋጌው ከተቀመጡት ማክበጃዎች ሁለቱ ተሟልቶ ከተገኘ፣ | 7 | 5 |
| | ደረጃ 4 | ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ በድንጋጌው ከተቀመጡት ማክበጃዎች ሶስቱም ተሟልቶ ከተገኘ፣ | 9 | 6 |
| 557 | በ557 ያለው ማቅለያ ተሟልቶ በተገኘ ጊዜ በ556 የሚያስቀጣው ቅጣት እርከን ከዚህ በታች በቀረበው መሰረት ይሆናል፡፡ | | | |
| 556 | | | | |
| | ደረጃ 1 | የደረሰው ጉዳት በ555 ወስጥ የሚወድቅ ቀላል ጉዳት ከሆነ፣ | 2 | |
| | ደረጃ 2 | ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ በድንጋጌው ከተቀመጡት ማክበጃዎች አንዱ ተሟልቶ ከተገኘ፣ | 3 | |
| | ደረጃ 3 | ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ በድንጋጌው ከተቀመጡት ማክበጃዎች ሁለቱ ተሟልቶ ከተገኘ፣ | 4 | |
| | ደረጃ 4 | ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ በድንጋጌው ከተቀመጡት ማክበጃዎች ሶስቱም ተሟልቶ ከተገኘ፣ | 5 | |
| 558 | ከጥፋተኛው ሀሳብ በላይ የደረሰ ጉዳት | | | |
| | ደረጃ 1 | ሊድን የሚችል የአካል ጉዳት ያደረሰ፣ | 5 | |
| | ደረጃ 2 | 1. አንዱን አካል ያጎደለ ወይም<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ ሟዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣ | 6 | |
| | ደረጃ 3 | 1. አስፈላጊ ብልቱን ያጎደለ፣ በሽታ እንዳይዘው ያደረገ ወይም<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ ሟዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣ | 6 | |

| የወንጀል ህጉ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት ማሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ ማሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| | ደረጃ 4 | 1. ሚስጢሩን ያበላሸ ከሆነ ወይም<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ መዋዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ | 7 | |
| | ደረጃ 5 | 1. በሰውነቱ ወይም በአእምሮው ለዘውትር ጠንቅ ያተረፈ (ሰርቶ መበላት እንዳይችል ያደረገው) ወይም<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 4 የተመለከተው ሆኖ መዋዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣ | 7 | |
| | ደረጃ 6 | 1. የተጎጂውን ህይወት የሚያሰጋ ከሆነ ወይም<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 5 የተመለከተው ሆኖ መዋዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣ | 8 | |
| | ደረጃ 7 | ድርጊቱ በደረጃ 6 የተመለከተው ሆኖ መዋዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣ | 9 | |
| 559 | **በቸልተኝነት የሚፈጸሙ የአካል ጉዳቶች** | | | |
| 559 (1) | | | | |
| | ደረጃ 1 | ቀላል የአካል ጉዳት | 2 | 1 |
| 559(2) | | | | |
| | ደረጃ1 | ሊድን የሚችል የአካል ጉዳት ያደረሰ፣ | 5 | 2 |
| | ደረጃ 2 | 1. አንዱን አካል ያጎደለ ወይም<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ መዋዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣ | 6 | 3 |
| | ደረጃ 3 | 1. አስፈላጊ ብልቱን ያጎደለ፣ በሽታ እንዲይዘው ያደረገ ወይም<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ መዋዊ ግዴታ ያለበት | 6 | 3 |

| የወንጀል ህጉ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| | | ከሆነ፣ | | |
| | ደረጃ 4 | 1. ሚስኩን ያበላሸ ከሆነ ወይም<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ ሞዋዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ | 7 | 4 |
| | ደረጃ 5 | 1. በሰውነቱ ወይም በአእምሮው ለዘወትር ጠንቅ ያተረፈ (ሰርቶ መብላት እንዳይችል ያደረገው) ወይም<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 4 የተመለከተው ሆኖ ሞዋዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣ | 7 | 4 |
| | ደረጃ 6 | 1. የተጎጂውን ህይወት የሚያሰጋ ከሆነ ወይም<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 5 የተመለከተው ሆኖ ሞዋዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣ | 8 | 5 |
| | ደረጃ 7 | ድርጊቱ በደረጃ 6 የተመለከተው ሆኖ ሞዋዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣ | 9 | 6 |
| 560 | **የእጅ እልፊት** | | | |
| | ደረጃ 1 | እጅ እልፊት | 2 | 1 |